# ***የዳያስፖራዉ ፖለቲካ ቆሽሿል - ተሃድሶ ይሳፈልጋ***

***አማኑዕል ዘሰላም*** *amanuelzeselam@gmail.com*

ፌብሩዋሪ 1 2013 FBI

*«ESAT is tasked to produce **accurate and balanced news** and information» ይላል የኢሳት ዔዲቶሪያል ፖሊሲ። ኢሳትን የሚያዳምጠዉ ሰው ጥቂት እንደማይሆን አስባለሁ። እስቲ በኢሳት የሚተላለፉ ፕሮግራሞችን እንመዝናቸዉ። ምን ያህል ሚዛናዊ፣ በእዉነት ላይ የተመሰረተ፣ የሁሉን ወገኖች አስተያየት ያንጸባረቀ ዜናና ትንታኔ ይቀርባል ? ምን ያህል በአገራችን ኢትዮጵያ መቀራረብ፣ ፍቅር፣ አንድነት እንዲሰፍን ይረዳል ?*

በቅርቡ ኢሳት አንድ ዘገባ አወጣ። «የ FBI መርማሪዎች፣ አበበ ገላዉን ለመግደል የታቀደን ሴራ አከሸፉ። በሴራዉ የተሳተፉ የሕወሃት ሰላዮች ምርመራ እየተደረገባቸው ነዉ » ሲል፣ በቦስተን፣ አቶ አበበ ገላው ላይ፣ የግድያ ሙከራ ለማድረግ እንደታሰበ እና ኤፍ.ቢ.አይ ሙከራዉን/ሴራዉን/እቅዱን እንዳከሸፈው ነበር ኢሳት የገለጸዉ።

ዜናዉን ተከትሎ ብዙዎቻችን፣ነፍጥ የያዘ ግለሰብ በስብሰባው ተገኝቶ ለመግደል ሙከራ ያደረገ ነበር የመሰለን። በዜናዉም በጣም አዘንን። ድርጊቱን ፈጸሙ የተባሉ፣ ነዋሪነታቸው በስተን የሆኑ፣ ጉሽ አበራ የተሰኙ ኢትዮጵያዊ ፎቶግራፍ በኢሳት ድህረ ገጽ ላይ ተለጠፈ። እኝህ ሰው እንደ ነፍሰ ገዳይ ተቆጠሩ። አገር ሁሉ አወቃቸው። እርግማንና ስደብ ወረደባቸው። ስማቸዉ ጠፋ። የፖለቲካ ጥገኝነት እንደጠየቁ፣ አቶ አበበ ገላዉን እንዲገድሉ በገዢዉ ፓርቲ እንደተላኩ፣ እንደ ኢሳት አባባል የሕወሃት ሰላይ እንደሆኑ፣ ቤታቸው እንደተበረበረ፣ እንደታሰሩም የሚገልጹ ዘገባዎችን በስፋት አነበብን፣ ሰማን።

የአቶ መለስ አፍቃሪ እንደመሆናቸው፣ አቶ ጉሽ ፣ በአቶ አበበ ገላዉ ላይ ንዴት ሊኖርባቸው ይችላል። በዚህም ምክንያት «አቶ አበበን መግደል ነበር» የሚል ስሜታዊ አስተያየቶችን በፌስ ቡክ ላይ ሳይለጥፉ እንዳልቀረ አስባለሁ። ( በነገራችን ላይ በተለያዩ ጊዜያት በጻፍናቸው ጽሁፎች ተናደዉ የተለያዩ የማስፈራራትና የዛቻ ኢሜሎች፣ እኛም ብዙ ጊዜ ደርሶናል)

የአቶ ጉሽን ስሜታዊና መነገር የሌለበትን አስተያየት (አቶ ጉሽ እራሳቸዉ እንደተናገሩ ያመኑት) ፣ ማንነታቸው ይፋ ያልወጣ፣ አንድ ወይንም በርካታ ግለሰቦች፣ ይቀዱና ለ FBI ይልካሉ መሰለኝ። ማናቸዉንም አይነት ማስፈራራትና ዛቻ፣ እንደ ትንሽ ነገር የማይቆጥረው FBI ፣ ሁኔታዉን ለመከታተል፣ መስሪያ ቤታቸው ድረስ በመምጣት ፣ አቶ ጎሽን ለአሥራ አምስት ደቂቃ የሚያህል አነጋገረ።

ነገሮች በተሟሟቁበት ወቅት፣ ለአሥርተ አመታት ሕዝብን በታማኝነት ያገለገለው የአሜሪካ ድምጽ ራዲዮ ጣቢያ፣ በዚህ ጉዳይ ላይ ሰፊ ዘገባ አቀረበ። አቶ አበበ ገላዉንና አቶ ጉሽ አበራን አወያየ። እዉነትን ሚዛናዊነት ባለው ሁኔታ መዘገብ ማለት ይሄ ነዉ። ከ FBI ባለስልጣናት፣ በጉዳዩ ላይ የተላከ ደብዳቤ ተነበበ። የግድያ ሙከራ ተፈጸመባቸው የተባሉት፣ አቶ አበበ ገላዉ የአየር ሰዓት ተሰጣቸው። ምንም አይነት የግድያ ሙከራ እንዳልተፈጸመባቸው ግልጽ አደረጉ። «ሴራ ነዉ እንጂ የግድያ ሙከራ አልተደረገም» ሲሉ ግን በኢሳት የተዘገበው ዜና ለመመከት ሞከሩ። FBI **የግድያ ሙከራ ለመደረጉና፣ ሴራ ለመጠንሰሱ የሚያሳዩ አንዳች አሳማኝ መረጃ እንዳላገኘ፣ በጉዳዩም የከሰሰው ማንም ሰው እንደሌለ፣ ለአሜሪካ ድምጻ ራዲዮ ጣቢያ አሳወቀ። እደግማለሁ እንደ** FBI **ገለጸ፣ ማናቸውም አይነት የግድያ ሙከራ አልተደረገም።**

ማንም ሰው በሕግ ወንጀለኛ ተብሎ እስኪወሰንበት ድረስ ጥፋተኛ አይደለም። አቶ ጉሽ አበራ በፌስቡክ የጻፉት ተገቢ ያልሆነና መታረም ያለበት መሆኑ እንደተጠበቀ፣ በፌስቡክ በጻፉት፣ እጅግ በጣም የከፋና የተጋነነ ወንጀል የሰሩ ይመስል፣ በርሳቸው ላይ ሳይጣራ፣ መረጃ ሳይኖር፣ በኢሳት አዝማችነት ዉርዥብኝ ደረሰባቸዉ። ያወቀም ያላወቀም ኢሳት ባናፈሰዉ ንፋስ እየተወሰደ አላስፈላጊ ነገሮች መናገር ጀመረ። ይህ በጣም አሳዛኝ ነዉ። ስህተትም ነዉ። በኢሳት ኢዲቶሪያል ፖሊሲ ቃል የተገባው ሚዛናዊነትስ የት አለ? ለምንስ ኢሳት አቶ ጉሽ አበራን አስቀድሞ ሳያነጋገርና ሳይጠይቅ፣ ሳያጣራም እርሳቸውን ይከሳል ? በዘፈቀደ፣ ያለመረጃ የዜጎች ስም እንዲጠፋ ማድረግ፣ ሊያስጠይቅ አይገባምን? ነዉር አይደለምን ? ለተፈጸመዉም ስህተት፣ አቶ ጉሽ አበራ እና የኢሳት አድማጮቹ የኢሳትን «ይቅርታ አደርጉልን፤ ተሳስተን ነበር» መልእክት ቢጠብቁ ተገቢ አይደለምን? **አንድ በሉ።**

ኢሳት «ብዙ የሕወሃት ሰላዮች» በምርመራ ላይ እንዳሉ ነበር የገለጸው ነዉ። ኢሕአዴግ የድርጅቱን የፖለቲካ ሥራ የሚሰሩ፣ ለአባይ ግንባታ መዋጮ እንዲሰበሰብ፣ በዳያስፖራዉ ዘንድ ኢሕአዴግ ተቀባይነት እንዲኖረው የሚረዱ ፣ የሚያሰማራቸው አባላት ይኖሩታል። ይሄ ደግሞ የሚጠበቅና ማንንም ሊያስገርም የሚገባ አይመስለኝም። ነገር ግን ኢሕአዴግ ሰዉን ለማስገደል፣ አህማዲኒጃድ እንዳደረገዉ፣ ወዳጅ በሆነችዉ በአሜሪካ፣ የግድያ ስኳድ (ቡድን) አሰማርቶ፣ ከአሜሪካ ጋር ያለዉን ግንኙነት ያበላሻል ብሎ ማሰብ፣ ኢሕአዴግን አለማወቅ ነዉ። ይቅርታ ይደረግልኝና፣ ኢሕአዴግ በዉጭ ሆነዉ በባዶ የሚጮኹትን ንቋቸዋል። ቦታም አይሰጣቸው። ምንም ማድረግ እንደማይችሉ፣ መተባበር እንዳቃታቸው፣ የአለም አቀፉ ማህበረሰብን ጆሮ ያላገኙ መሆናቸውን ጠንቅቆ ያውቃል።

**ኢሳት «የሕወሃት ሰላዮች» ሲል፣ ምን መረጃ ይዞ እንደዚያ እንዳለ አይገባኝም።** የኢሳት ባልደረቦች ለኢሕአዴግ ጥላቻ ስላላቸዉ ብቻ ፈጥረው ያወሩት እንጂ ኢሕአዴግ ሰላይ ስለመላኩ ፣ የላካቸውም ሰላዮች የግድያ ሴራ እየፈጸሙ ስለመሆናቸዉ ምንም መረጃ የላቸውም። አለን የሚሉ ከሆነ ደግሞ እስከአሁን ለሕዝብ የገለጹት ነገር የለም። «ሰላዮች» ብለው ሲሉም፣ ያዉም በስህተትና በችኮላ፣ አቶ ጉሽን ብቻ ነዉ እንጂ የጠቆሙት ሌሎችን አልዘረዘሩም። **ሁለት በሉ።**

የአሜሪካ ድምጽ ራዲዮ ባልደረቦች፣ ከደርግ ዘመን ጀምሮ፣ የኢትዮጵያን ሕዝብ ሲያገለግሉ የነበሩ፣ የተከበሩ የተወደዱ ወገኖቻችን ናቸው። ስራቸውን ጠንቅቀዉ የሚያውቁ፣ የጋዜጠኝነት ፕሮፌሽናሊዝም የተላባሱ ባለሞያዎች ናቸው። ከ FBI የተላከላቸውን ደብዳቤ ለአንባቢያን ማቅረባቸው እንደ ነዉር ተቆጥሮ፣ ሊያስወቅሳቸዉና ሊያሰድባቸው በቅቷል። በተለይም ጋዜጠኛ አበበ ገላዉን ጨምሮ ለዲሞክራሲና ለጋዜጠኖች ነጻነት እንቆማለን የሚሉ ወገኖች፣ በጋዜጠኛ ሄኖክ ሰማእግዚአብሄር ላይ ያነጣጠሩት ክስ አስገራሚ ነዉ። እነዚህ ወገኖች በሚሰብኩት የማይኖሩ፣ እነርሱ ሲናገሩና አስተያየት ሲሰጡ እንጂ፣ ከነርሱ የተለያ አስተያየት ያለዉን በተለይም እነርሱን ቻሌንጅ የሚያደርግን ሰው የማይታገሱ መሆናቸዉን ነዉ እያሳዩን ያሉት፡፡

ጋዜጠኛ ሆነ ማንም፣ ከኛ የተለየ አመለካከት ካለዉ፣ የኛን ሃሳብ ዉድቅ ካደረገ፣ ወይንም ለመቀበል ካዳገተው መብቱ መሆኑ መረዳት አለብን። ቢቻል ሃሳቦቻችን ተቀባይነት እንዲኖራቸዉ የበለጠ መረጃዎች በማስቀመጥና አቀራረባችንን በመቀየር ማሳመን እንሞክር። አለበለዚያም ላለመስማማት ተስማምተን (agree to disagree) መከባበር ይጠበቅብናል። እንጂ የሃሳብ ልዩነቶች አበሳጭተዉን፣ በስሜታዊነት ወደ ግለሰብ ጠብ ወይንም ስድብና ክስ ማምራት የለብንም። **ሶስት በሉ።**

በምርጫ ዘጠና ሰባት ወቅት ከቅንጅት መሪዎች ጋር ለሁለት አመት በቃሊቲ ማቀዋል። ከባድና ፈታኝ በሆነበት ሁኔታ፣ የግል ጋዜጣ ኤዲተር ሆነው በአገር ቤት ለበርካታ አመታት የኢትዮጵያን ሕዝብ አገልግለዋል። እርሳቸዉ የሚያዘጋጁት ጋዜጣ አዲስ ድምጽ፣ ኢ.ኤም .ኤፍ፣ አቡጊዳ፣ ኢትዮጵያሜዲያ በመሳሰሉ ድህረ ገጾች በነጻ ይወጣ ስለነበረ፣ በአገራችን ያለዉን ሁኔት በቅርበት እንድንከታተል ረድቶናል። የፓልቶክ ክፍሎችም ይህን ጋዜጣ በየሳምንቱ ያነቡ ነበር። ይህ ጋዜጣ የአዉራምባ ታይምስ ጋዜጣ ነዉ። ዋና አዘጋጁም አቶ ዳዊት ከበደ ናቸው።

አቶ ዳዊት ከበደ፣ ከጥቂት ወራት በፊት አቶ ያሬድ ጥበቡን ፣ በቅርቡ ደግሞ አቶ ጉሽ አበራን ቃለ መጠይቅ በማድረጋቸው «ወያኔ» ናቸው እየተባሉ ነዉ። በተለይም አባ መላ የሚባሉ ኢትዮጵያዊ የሚመሩት፣ የሲቪሊቲ ፓልቶክ ክፍል፣ እንግዳ ሆነዉ በመቅረባቸው፣ ብዙዎችን አስቀይመዋል። ለምን አባ መላ የኢሕአዴግ ደጋፊ በመሆናቸው !!! በዳያስፖራ አለን ከሚሉ ተቃዋሚዎች አመለካከት የተለየ አመለካከት ካላቸው፣ የኢሕአዴግ ደጋፊዎች ከሆኑ፣ ኢትዮጵያዉያን ወገኖቻችን ጋር አቶ ዳዊት መነጋገራቸው ወንጀል ሆኖ እያስከሰሳቸው ነዉ። **አራት በሉ።**

በኢሳት ፕሮፖጋንዳ አዝማችነት፣ በዳያስፖራ ስር የሰደደዉ ፖለቲካ፣  ምን ያህል የተበላሸና የቆሸሸ መሆኑን የሚያሳዩ ሌሎች ብዙ ምሳሌዎችን መዘርዘር ይቻላል።

እንደሚገባኝ፣ መሰረታዊ የሆነ የአስተሳሰብ ተሃድሶ መኖር እንዳለበት አስባለሁ። የዳያስፖራዉ ፖለቲካ ትልቅ ለዉጥ ያስፈልገዋል።  እንደ ኢሳት ያሉ፣  በኢዲቶሪያል ፖሊሲያቸው ቃለ የገቡትን ጠብቀዉ፣ እራሳቸዉን በማሻሻል፣ የጥላቻ ፕሮፖጋንዳ ማስፋፊያና የሻእቢያ መሳሪያ  ሳይሆኑ፣  የ21ኛዉ ክፍለ ዘመን የስለጠነ ፣ ዲሞክራስያዊ ሜዲያዎች ሊሆኑ ይገባል። አለበለዚያ  እነርሱን እያዳመጥን፣ በገንዘብ እየረዳን ፣ ሕዝባችንንና አገራችንን የሚጎዳ፣ የጥላቻ  መንፈስ በመካከላችን እንዲሰፍን መፍቀድ፣ እራሳችንንም በዚህ ቁሻሻ ፖለቲካ ማጨማለቅ የለብንም።

ምን አለ የመወጋገዝና የመካሰስ ፖለቲካ ተወግዶ የመወቃቀስና የመተራረም ፖለቲክ ቢሰፍን ? የፖለቲካ ልዩነቶች ይኖሩናል። አንዳችን የምንደግፈውን ድርጅት ሌሎች ሊቃወሙት ይችላሉ።  በሰለጠነ መንገድ መነጋገር ሲቻል እንዲሁ በባዶ ጦር መማዘዝ ምን ይበጃል?  አንድ ነገር መርሳት የለብንም። አገራችን ኢትዮጵያ ድህ አገር ናት። ብዙ የምንሰራዉ ሥራ አለ። ገና ረጅም መንገድ እንደ ሕዝብ መጓዝ አለብን። አሁን ባለው አይነት ሁኔታ፣ በዚህ በጥልቻ ድባብ ዉስጥ ግን  መቀጠል አንችልም። ፖለቲካችን መሰረታዊ የሆነ ተሃድሶ ያስፈልገዋል።አራት ነጥብ።

**እንደ ኢሳት ፣ ኢካዴፍ ያሉ ወገኖች ቆም ብለው እንዲያስቡ በአክብሮት እጠይቃለሁ። የሚዘግቡትን፣ የሚናገሩትን ይመርምሩ እላለሁ። የሚያፈርስ፣ የሚያራርቅ ሳይሆን አንድ የሚያደርግ፣ የሚያሰባስብ፣ የሚያስተምር ዘገባ ያቅርቡ። ኢሕአዴግን መቃወማቸውን ይቀጥሉ። ኢሕአዴግ የሚሰራቸው ስህተቶች ያጋልጡ። ነገር ግን በስሜታዊነትና በጥላቻ ሳይሆን በሰለጠነ መንገድ ያድርጉት። ኢሕአዴግን እንደሚቃወሙትም ሁሉ፣ ኢሕአዴግ ለሚያደርጋቸውም መልካም ተግባራት እውቅና ይስጡ።**

መቼም ኢሕአዴግ ምንም የሰራው ሥራ የለም ብሎ የሚከራከር፣ ወይንም የሚያምን ሰው ይኖራል ብዬ አላስብም። ምንም እንኳን በመልካም አስተዳደር፣ በሰብዓዊ መብት መከበርና በዲሞክራሲ ግንባታ አንጻር፣ በዘጠና ሰባት ከነበረዉ  በጣም ያሽቆለቆለ ሁኔታ ላይ ብንገኝም፣ በልማቱ አንጻር አስደሳች ዉጤት እየተመዘገቡ ነዉ። ግልገል ጊቤን፣ በለስ፣ ተከዜ፣  አባይ የመሳሰሉ ግድቦችን፣ ሊሰሩ የታሰቡ የባቡር ሃዲዶችን፣ መንገዶችን፣ ዩኒቨርሲቲዎችን፣ የጤና ጣቢያዎችን የመሳሰሉትን መጥቀስ ይቻላል። የሚታዩ ፣ የተጨበጡ ለዉጦች በአገራችን እየታዩ ነዉ። ይሄ መደገፍ፣ መበረታታ አለበት።

በዉጭ ግንኙነት አንጻር በሶማሊያና በሱዳን ኢትዮጵያ የተጫወተችዉና እየተጫወተችዉ ያለዉ ሚና እንደ ኢትዮጵያዊ የሚያኮራ ነዉ። ለዚህም ኢሕአዴግ ሊመሰገን ይገባዋል።

ኢሕአዴግ ስላከናወናቸው መልካም ተግባራት መዘገብ፣  ከአሁን ለአሁን «ኢሕአዴግ መጥቀም ነው» በሚል ኢሳቶች እዉነትን መደበቅ የለባቸው። የኢሕአዴግን መልካም ተግባራት ለመዘገብ መድፈርና መቻል አለባቸው። በኢዲቶሪያል ፖሊሲያቸዉ የሁሉን አመለካከቶች እናስተናግዳለን አይደለም እንዴ የሚለው ? አዲስ ነገር አይደለም የምጠይቀዉ። ፖሊሲያቸው ላይ ያለውን በተግባር ያዉሉት ነዉ የምለዉ።

Comment [I1]:

**Comment:**

Zelalem, you know we have not lost hope with you yet thus why we have decided to post your latest commentary. After all these years you should know these extremists are up to no good. Ethiopia's democratic aspiration can only be enhance if we collectively defeat these few

extremists and open the playing field for those matured and good meaning political forces. Stop begging and cajoling these people. We declined many articles and commentaries in regard to the smear campaign against Guish simply because we thought the despicable were yearning for such coverage. Now that the euphoria has come and gone we have decided to post so that it gives us a reason to tell you the following so that next time you will consider it to use "...Qomata Qomata Kalalut Gebto Yifetefetal," We plead you not to embolden these extremists by giving them space in the democratic forum! Thank You. Aigaforum, Feb 1, 2013